# እንኳን ለ 2010 አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ



ኢሳ 43፡13 እሰራለሁ የሚከለክለኝ ማን ነው? መዝ 119፡126 ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ ነው፡፡

ንጉስ ሰለሞን በመክብብ 3፡4 ላይ ለመስራትም ጊዜ አለው ይላል፡፡ እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ ሥራ ያቆመበት ጊዜ የለም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ስለዚህ ሲናገር አባቴ እስከ ዛሬ ይሰራል፣ እኔም እሰራለሁ ብሎአል፡፡ እግዚአብሔር ሥራ ያልሰራ ሥራውን ያቆመ የመሰለባቸው ጊዜያት ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚያ ጊዜያት እንኳን ለጌታ የሥራ ጊዜያት ነበሩ፡፡እግዚአብሔር ሥራውን በሁለት ዓይነት መንገድ ይሰራል፡፡ አንዱ በግልጽ የሚሰራበት ሲሆን ሌላው በስውር የሚሰራበት ነው፡፡

ባለፉት ዓመታት እግዚአብሔር በቤተክርስቲያናችን ውስጥ በስውርና በግልጽ የሰራቸው ሥራዎች አያሌ ለመሆናቸው ሁላችንም ምስክሮች ነን፡፡ ይህ በፊታችን ያለው ዘመን ግን እግዚአብሔር በግልጽ ሥራውን የሚሰራበት ለየት ባለ መልኩ እንደሚሆን አምናለሁ፡፡

በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጌታ በግልጽ ሥራውን የሚሰራበት ዘመን ሲደርስ የሰዎች ሕይወት በሚያስገርም ሁኔታ ሲለወጥ፣ ሰዎች ከሥጋም ሆነ ከመንፈሳዊ ችግራቸው ሲፈቱ፣ ተዓምራቶችና ድንቆች ፣ ትንቢቶች፣ ራዕዮችና መገለጦች ለየት ባለ መልኩ ሲመጡ ቤተክርስቲያን ከአንድ ክፍል ወጥታ ከተማዎች ፣ አገሮችና ዓለም አቀፍ ሥራዎች እንደተሰሩና ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች እንደተነሱ ማስተዋል እንችላለን፡፡

ይህ በፊታችን ያለው ዓመት ለቤተክርስቲያናችንም ሆነ በዓለም ዙሪያ ላለችው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እነዚህን ታላላቅ ሥራዎች የምታይበትና የምትሰራበት ዘመን እንደሚሆን እምነቴ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ በክብር ከመመለሱ በፊት እድፍና የፊት መጨማደድ ለሌለባት ብርቱና ኃይለኛ ቤተክርስቲያን እንደሚመጣ ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 5 ይነግረናል፡፡

በአዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ ቆመን ላለን ሁላችን ለዚህ ታላቅ የእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ እንድንነሳና አብረን የጌታን ሥራ እንድንሰራ ታላቅ ጥሪዬን እያስተላለፍኩ መጪው ዓመት የደስታ፣ የበረከትና የሥራ ዓመት እንዲሆንላችሁ በራሴና በቤተክርስቲያኒቱ ስም መልካም ምኞቴን አስተላልፋለሁ፡፡

መልካም ገናና አዲስ ዓመት ለሁላችሁ ይሁን!

ኢዮ 42፡2 ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ ነህ፣ ሀሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል ወቅሁ፡፡

መጋቢ እንድርያስ ሐዋዝ